# በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት በስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ ትግበራና ክትትል ቡድን በ2014 ዓ/ም የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ዉጤት ለማሻሻል /ለማሳደግ/ የተዘጋጀ የንቅናቄ ሰነድ ፡፡

ህዳር 2014 ዓ/ም

# መግቢያ፡-

የተማሪዎች ዉጤት ማሳደግና መሻሻል ከትምህርት ጥራት ማረጋገጫ አመላካች ዋነኛዉ መሆኑ ይታወቃል ። ይህ የተማሪዎች ዉጤት ከክፍል ፈተና ባለፈ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥና ደረጃዉን የጠበቀ ፈተና ተዘጋጅተዉ ተማሪዎች ይፈተናሉ ዉጤታቸዉም እንደሁ በክልልና በሀገር አቀፍ ደረጃ ይተነተናል ይገመገማል። ይህንን የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ፈተና ዉጤት ግምገማና ትንተና መነሻ በማድረግ የአሰራር ጥንካሬንና ክፍተቶችን በመለየት የተማሪዎችን ዉጤት ለማሳደግና ለማሻሻል የተለያዩ አሰራሮችን፣ ስልቶችን፣ መድረኮችን፣ እቅዶች በማዘጋጀትና የጋራ አድርጎ ወደ ተግባር በመቀየር የተማሪዎችን ዉጤት ማሳደግ ብሎም ሀገራዊ ትምህርት ፖሊስ ግቦችን ማሳካት ያስፈልጋል። ከእነዚህ ስልቶችና እዶች ለ2014 ዓ/ም የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ዉጤት ለማሳደግ የአንድ ጌፅ እቅድ ተዘጋጅቷል።

# ዓላማ፡-

- ይህ የ2014 ዓ/ም የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት ማሰደጊያ/ማሻሻያ/ ንቅናቄ ሰነድ የምከተሉትን ዓላማዎች አንግቧል፡-

- ➢ አሁን ያለንበት የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት ላይ መስማማት
- ➢ የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት ለማሳደግ በደረጃዉ የተቀየሱ ስልቶችና የአንድ ጌፅ እቅድን የጋራ ማድረግ
- ➢ የተማሪዎችን ዉጤት ማሳደግ የሚችሉ አሰራችን ለይቶ ማወቅና ተግባራዊ ማድረግ
- ➢ የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት ለማሳደግ ተጨማሪ ስዎችንና ሰዓቶችን መጠቀም እንዳለብን መግባባት
- ➢ የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት የትምህረት ፖሊሲዉ ያስቀመጠዉን ግብ ማሳካት መቻል።

# ነባራዊ ሁኔታ ዳሰሳ፡-

- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ዉጤት ለማሳደግ ባለፉት ዓመታት በርካታ ተግባራትን ሲያከናዉን ቆይቷል ለምሳሌ፡-አንድ ጌፅ እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሰደረግ ቀይቷል፣መማር ብቃትን መሰረት ያደረገ ተከታታይ ምዘና ቅፅ በክፍለ ከተማ ደረጃ በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረግን እንገኛለን፣ደረጃዉን የጠበቀ ሞደል ፈተና በማዘጋጀት በዓመት ሁለት ጊዜ እንድፈተኑና ራሳቸዉን እንድገመግሙ ተደርጓል፣ሰፋፍ ክትትልና ድጋፎችን በማድረግ የተለያ ግብረ መልሶችን መስጠተወ ተችሏል፣የተወሰኑ አቅም መገንብያ ስልጠናዎችን መስጠትም ተችሏል፡፡

# ነባራዊ ሁነታ ዳሰሳ

- እነዚህ ተግባራት ብከናወኑም የተማሪዎች ዉጤት በምፈለገዉ ደረጃ ግን አላደገም። ለእነዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ ባለፉት ዓመት በኮሮነ በሽታ ምክንያ የትምህርት አሰጣጡ ላይ ትልቅ የምባል ጫና ማሳደሩ፣ችግችን በጥናትና ምርምር ያለ መፍታት፣ዉጤት ተኮር ስልጠናና ክትትል ያለማድረግ፣የመምህራን የትምህርት ባለሙያዎች ተነሳሽነት ማነስ፣የምዘና ስረዓት በሳይንሱ መሰረት ያለመከናወን፣ትምህረት በተግባር በስጠት ላይ ክፍተቶች መኖራቸዉ፣በሁሉም ደረጃ ተጨማር ስራዎችን ያለመስራት፣ተጨማር ሰዓትን ያለመጠቀም እና የተለያዩ የአሰራር ክፍተቶች በተማሪዎች ዉጤት ላይአሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል። ስለሆነም በ2014 ዓ/ም እነኝህን ክፍተቶችና የአሰራር ግድፈቶችን አሻሽሎ የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል የተማሪዎችን ዉጤት ማሳደግ ያስፈልጋል።

## በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት 8ተኛ ክፍል ማሳለፊያ ምጣኔ፡፡

| ተ.ቁ | 2011 ዓ/ም | | | 2012 ዓ/ም | | | 2013ዓ/ም | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈተኑ | ያለፉ | መቶኛ | የተፈተኑ | ያለፉ | መቶኛ | የተፈተኑ | ያለፉ | መቶኛ | |
| 1 | 2534 | 2328 | 91.9% | 2266 | 2131 | 94.0% | 2390 | 2296 | 96.1% | |

# በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት 8ተኛ ክፍል 50% በላይ ያመጡ።

| ተ.ቁ | 2011 ዓ/ም | | | 2012 ዓ/ም | | | 2013ዓ/ም | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የተፈተኑ | >50 % | መቶኛ | የተፈተኑ | >50 % | መቶኛ | የተፈተኑ | >50 % | መቶኛ | |
| 1 | 2534 | 1328 | 46.8 % | 1256 | 2131 | 48.2% | 2390 | 1173 | 49.1 % | |

# በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ት/ጽ/ቤት 8ተኛ ክፍል 50% በላይ በትምህርት ዓይነት፡፡

| 2013 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ውጤት በየት/ት ዓይነት ትንተና (በአማርኛ ቋንቋ የተፈተኑ) | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የት/ት ዓይነት | የተፈተኑ | | | ከ50% በታች ያመጡ | | | ከ50% በላይ ያመጡ | | | በመቶኛ |
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | |
| አማርኛ | 1099 | 1289 | 2388 | 105 | 149 | 254 | 994 | 1140 | 2134 | 89.4 |
| እንግሊዘኛ | 1116 | 1315 | 2431 | 747 | 973 | 1720 | 369 | 342 | 711 | 29.2 |
| ሂሳብ | 1100 | 1289 | 2389 | 896 | 1129 | 2025 | 204 | 160 | 364 | 15.2 |
| ባይሎጂ | 1100 | 1289 | 2389 | 712 | 883 | 1595 | 388 | 406 | 794 | 33.2 |
| ፊዚክስ | 1100 | 1289 | 2389 | 791 | 1009 | 1800 | 309 | 280 | 589 | 24.7 |
| ኬሚስትሪ | 1100 | 1289 | 2389 | 699 | 848 | 1547 | 401 | 441 | 842 | 35.2 |
| ሶሻል ሳይንስ | 1100 | 1294 | 2394 | 585 | 752 | 1337 | 515 | 542 | 1057 | 44.2 |
| ስነ ዜጋና ስነምግባር | 1101 | 1289 | 2390 | 19 | 17 | 36 | 1082 | 1272 | 2354 | 98.5 |

# ትንተና

- ከላይ በሰንጠረጆች ማየት እንደምቻለዉ ከ2011 እስከ 2013 ዓ/ም የማለፍ ምጠነዉ እና ከ50 በላይ የስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር በትንሹም ብሆን እየጨመረ  ይገኛል፡፡ ይሁንና በፖሊስ ላይ የተቀመጠዉን ግብ ለመድረስ ገና ግማሽ መንገድ ላይ እንገኛለን ፡፡

# ትንታና---

- ከላይ በተጠቀሰዉ መሰረት ስነ ዜጋና ስነምግባር ት/ት 98.5%፣ አማርኛ 89.4% አማካኝ 50 እና በላይ የመጣበት የት/ት ዓይነት ሲሆን
- **እንግሊዘኛ 29.2%፣ ፊዚክስ 24.7%** እና **ሂሳብ 15.2%** አማካኝ 50 እና በላይ የመጣባቸዉ የት/ት ዓይነቶች ናቸዉ።
- እንግሊዘኛ ት/ት ዓይነት በሁለቱም ቋንቋ ስርዓተ ት/ት የተቀመጠ ነዉ።
- የሳይንስ ት/ቶች ላያ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚደገባ ያሳያል።

❖ 12ተኛ ክፍል ዉጤትን በተመለከተ ለ8ኛ ክፍል የተጠቀምነዉ ነባራዊ ትንታነ በ2012 ዓ/ም 350 በላይ ያስበዘገቡ 56.2 በመቶኛ ስሆኑ ገና ብዙ መስራት እንደምጠበቅብን ያሳያል።

# የ2014ዓ/ም እቅድ፡-

ከላይ የተመዘገቡትን የ8ኛ 12ኛ ክፍል ዉጤት መነሻ በማድረግና በእጃችን ያለዉን መልካም አጋጣሚዎችን በመጠቀም የሚከተሉትን አቅዶች ማዘጋጀት ተችሏል፡-

1)ሁሉም የ8ተኛ ክፍል ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች 50 እና በላይ እንድያስመዘግቡ ማድረግ፡፡

2)ሁሉም የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች 350 እና በላይ እንድያስመዘግቡ ማስቻል፡፡

- ይህንን አቅድ ለማሳካት የ2014 ዓ/ም የ1ጊፅ አቅድ የተዘጋጀ ስሆን እንደምከተለዉ ቀርበዋል፡-

# በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህረት ጽ/ቤት በስርዓተ ትምህርት አጠቃላይ ትግበራና ክትትል ቡድን የ8ኛ እና የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችዉጤት ማሻሻል እንድያስችል የሚከናወኑ ተግባራት

| ተ.ቁ | የሚከናወኑ ተግባራት | የክንዉን ጊዜ | ፈፃሚ አካል | በኃላፊነት የሚያስፈፅም | የሚጠበቅ ዉጤት | የሚያስፈልግ ግበዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በየደረጃዉ በእቅዱ ላይ ዉይይት ማድረግና ግበዓት ማሰባሰብ | ህዳር 06/14 | ስርዓተ ት/ት ቡድን | የጽ/ቤት ኃላፊ | በተዘጋጀዉ የድርግት መረሃ ግብር ዙሪያ የጋራ መግባባት ላይ ተደርሰዋል | ለተሳታፊዎች አበል |
| 2 | በየደረጃዉ ካሉ ስ/ት/ት ባለሙያዎች ጋር ዉጤቱ ያለበትን ደረጃ ላይ ዉይይት ማድረግ | እስከ ህዳር10 /14 | >> | >> | በት/ት ዓይነቱ የክ/ከ ዉጤት ያለበትን ደረጃ ማወቅና የመፍትሄ ሀሳቦችን ማስቀመጥ | ለተሳታፊዎች አበል |
| 3 | የ2013 ዓ/ም የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ዉጤት ትንተና መሰረት ያለንበት ደረጃ መወሰን | እስከ ህዳር 13/14 | >> | >> | በት/ት ዓይነቱ ያለዉን ዉጤት አፈፃጠም ለይቶ መፍትሄ ማስቀመጥ | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |
| 4 | የተማሪወ ወላጅ ማህበርና መ/ረና ማህበርየተማሪዎችን ዉጤትለመሻሽል ንቅናቄበማዘጋጀት ወደ ስራ ማስገባት | ህዳር 16-17 መጋቢት 17-18/14 | >> | >> | የህብረተሰብ ተሳትፎን በማሳደግ የተማሪዎችን ዉጤት ማሻሻል | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |

# የቀጠለ---

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | ለተማሪዎች የአጠናን ስልት ስልጤና መስጠት | ህዳር 22-23/14 | >> | >> | ተገቢዉን የጥናት ስልት ያዉቃሉ | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |
| 6 | በፈተና አዘገጃጀት ዙሪያለመ/ራን የግንዛቤ ማስጨበጫ TOT መስጠት | ህዳር 24-25/14 | >> | >> | መራን በሚያስተምሩት ት/ት ተገቢዉን የምዘና ስርዓትን እንድያስተገብሩ ያስችላል | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |
| 7 | ለተማሪዎች በትምህርታቸዉ ዙሪያ የማነቃቂያ መረሃ ግብር ማዘጋጀት | ህዳር 25-26/14 | >> | >> | ትምህርታቸዉን በዓግባቡ ትኩረት በመስጠት ይከታተሉታል | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |

# የቀጠለ---

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | በሁሉም የ8ኛና የ12ኛ ክፍሎች ላይ ትርጉም ያለዉን የክትትልና ድጋፍ ማድረግ | ከህዳር 27/14 ጀምሮ | >> | >> | አጠቃላይ ስራዉ ያለበት ሁኔታን በመገምገም ዉሳኔ ያስቀምጣል | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |
| 9 | ተማሪዎች ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በተገቢዉ መንገድ እንድማሩ ክትትል ድጋፍ ማድረግ ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ምገባ ማዘጋጀት | ከህዳር 27 ጀምሮ | >> | >> | ተማሪዎች ተገቢዉን ት/ት በተገቢዉ ጊዜ እንድያገኙ ማድረግ | ለተሳታፊዎች ዉሎ አበል |
| 10 | ለተማሪዎች በሳምንት አንድ ቀን የፈተና ቀን እንድሆን ማድረግና በየደረጃዉ ሞደል ፈተና በማዘጋጀት እንድፈተኑ ማድረግ | ከህዳር 27 ጀምሮ | >> | >> | ተማሪዎች እራሳቸዉን እየመዘኑ ዉጤታቸዉን እንዲያሻሽሉ ማድረግ | ለሞደል ፈተና አዘጋጆች ዉሎ አበል |
| 11 | በየደረጃዉ ወርክሺት እንድዘጋጅ ማድረግ እና ተተኳር የት/ት ዓይነቶች ላይ በትኩረት መስራት | ከህዳር 27 ጀምሮ | >> | >> | ተማሪዎች ትኩረት የሚፈልጉ ነጥቦች እንድረዱና እንድገነዘቡ ማድረግ | --- |

# [illegible]

- የ8ተኛና የ12ተኛ ክፍል ተማሪዎች ዉጤት ለማሳደግ ተግባራትና አሰራር ስርዓቶች በቤጀት ልታገዙ ይገባል ፡፡ ስለሆነም ሁሉም የቤጀት ባለበቶች ለዚህ ተግባር አስፈላጊዉን የቤጀት ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል እንድሁም የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም መምህራን ማህበር፣ተማሪ ወላጅ ማህበር፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ይህንን ተግባር በፋይናንስ ማገዝ አለባቸዉ፡፡

# ማጠቃለያ

- ይህ ሰነድ ዉጤታማ የሚሆነዉ ሁሉም የትምህርት ማበረሰቡ፣የትምህርት አመራሮች፣ባለሙያዎችና መምህራን አምነዉ ስቀበሉና ወደ ተግባር ስቀይሩት ነዉ። ስለሆነም ሁላችንም የተማሪዎችን ዉጤት ለማሻሻልና ሀገራዊ የትምህርት ግቦችን ለማሳካት ስንረባረብ ብቻ ነዉ።

አመሰግናለሁኝ